በተስፋ አሥራ አንደኛው

ይፍቱሥራ ምትኩ



በተስፋ አሥራ አንደኛው

ይፍቱሥራ ምትኩ

2014 ዓ.ም

Walia publisher
ዋልያ አሳታሚ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All right reserved!
በተለይ አሥራ አንደኛው
ይፍቱሥራ ምትኩ
አዲስ አበባ ÷ ኢትዮጵያ
yiftunard@gmail.com

የመጀመሪያ አትም - ሰኔ 2014 ዓ.ም

መታሰቢያነቱ

የጥበብ ቅን ወዳጅ ለሆነው ለወዳጄ እዝራ አብደላ ይሁንልኝ!
ነፍስ ኄር!

የሽፋን ሥዕል - አንዱ ጌታቸው (0932178722)
የሽፋንና የውስጥ ገጽ ቅንብር - አዛርየስ ደሴ (0935854117)

አሳታሚና አከፋፋይ - ዋልያ አሳታሚና መጽሐፍ መደብር
0956560000 / 0966252525
አዲስ አበባ ÷ አራት ኪሎ ÷ ኢክላስ ሕንጻ

ለአንዲቱ

ለወዲቱ

ለአቲጌይቱ

ልጅ

የኔ ናርዶስ

ላንቺ ስጦታ ነው!

ምስጋና

ብዙዎች ህልማቸውን ለማስረዳት በሚለፋባት ዓለም፥ ያላብራራሁትን ህልሜን የፈታችሁልኝ

አቶ ክቡር ገና (በፊትህ እንደታናሽ ስቆም እንደታላቅ ያከበርከኝ!)

ወ/ሮ ሲቲ ሁሴን (ህልማችንን ብዙዎች ያደንቃሉ። ትርጉም የሚያሰጡት ግን ጥቂቶች! አንዷ አንቺ ነሽ!)

መምህር መሰረት አበጀ (ጽሑፉን በማንበብና በማረቅ፥ ደፍሬ እንድወጣም ያበረታኸኝ ጋሼ፥ እኔ ልጅህ ለቅን ልብህ እጅ እነሳለሁ!)

ጋዜጠኛ ታምሩ ከፈለኝ (ወዳጅነት ጊዜ መቁጠር አለመሆኑን ባንተ አየሁ!)

ሩት ሃ/ማርያም (እግዜር መቼም ታምሩ አያልቅ፥ እንደአዳም በጥልቅ እንቅልፍ ሳይጥለኝ ከጎኔ አንቺን የመሰለች ውብ እህት ያኑርልኝ? ምን ይባላል ለዚህ?)

አዛርየስ ደሴ (ያንተ የእያንዳንዱ ቀን አብሮነት (ስንት'ዜ መንገድ እንዳላስተላለፈን፥ በአዲስ አወዳጅቶን ይሄ ሥራ) ከምንም በላይ አበርትቶኛል። ክብር ለታናሽ ወንድምነትህ!)

'ሀብቴ ህዝብ ነው' ሲባል ቀልድ የሚመስላችሁ ሁሉ እኔ የሰው ሃብታም እዚህ ስም ለመጥቀስ ጀምሬ ስንተባተብ ባያችሁ?!

ብዙ ነገር ፈልጌ አላውቅም። ለውስን ፍላጎቴ ግን ህይወት ብዙ በረከትን ሰጥታኛለች። ከመኖር ያተረፍኩ፥ ሰዎች በክፉዎች በሚፈተኑባት ዓለም በደጋግ ሰዎች ተከብቤ የተፈተንኩ ነኝ።

ሰዎቼ፣ እዚህ'ዎቼ፣ እዛዎቼ፣ ሳቄንም እንባዬንም የምታውቁ 'ማንም' ሆኜ ሳለሁ 'እከሊት' እንደሆንኩ ህልው ያደረጋችሁኝ፣ ሰማዮቼ፣ ምድሮቼ... በመኖሬ ያገኘኋችሁ ሁሉ... ሁላችሁ ሁላችሁ... ብዕር ለካ ይሰንፋል ለፍቅር...?!

ለሁላችሁ አንድ አንድ ልብ አለኝ!
ክበሩልኝ!

ጀበና ⑨ / በተሰይ አሥራ አንደኛው ㉗ / ቀቤ ㊶ / አልቴት ㊼

ጣሪያ ㊶ / አርብ አርብ ይሸበራል ልቤ ㊾ / ቀለም ㊼ / ምልዓት ㊿



ከወላጅ እናቴ የተነጠልኩት እንዲህ ነበር።

"ለማጂና አልማጂ ደህና ሁኑ!"

ይህንን ስትል እጇ ላይ የነበረውን የዳቦ ፍርፋሪ በትኜ ማልቀስ ጀመርኩ። ዞራ አላየችኝም። የሳሎኑ በር ክፍት ነበር። ጀርባዋ የሚራመድ ጥላ ሞት ሆኖ ይታየኛል። ጩኸት ጨመርኩ ለቅሶዬ ላይ። በሩን አለፈች፥ የግቢውን በርም። ወደግራ ታጥፋ ዞር ብላ ያየችኝ ይመስለኛል።

ዝም አልኩ።

ሶስት ዓመቴ ነበር።

* * *

ዘመናይ ሴት ነኝ አሁን። ኑሮና ዘመን ያዘመነኝ። እንዲህ ሳስበው ካልሆነ ቁመናዬን አይቶ መጀሌዬን፥ አለባበሴን አይቶ ቆንጥር የተጫወተብኝ እንደሆንኩ ማንም አይገምትም።

"የገጠር ልጅ ነኝ" ስላቸው

"ሂ . .ሂ . .ሂ . .አትመስይምኮ ግን. . .ሃ. . .ሃ. . .ሃ"

"እንዴ መጀሌ አይደል ያሳደገኝ"

"ስሙንም ታውቂያለሽ? ተይ አትቀልጂ። ማን ነገረሽ ስለሱ እናቴ? ሃ. . .ሃ. . .ሃ"

"አማርኛዬ ራሱ. . ." አያስጨርሱኝም
"ምን ይወጣለታል አማርኛሽ... ሂ . .ሂ . .ሂ"

ማንነትን መነጠቅ ከዚህ ይለያል?

Walia publisher
ዋጋ 199.00 ብር